የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ — የካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 6
ADDIS ABABA – 13th February, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
ለብሔራዊ የማዳበሪያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ...................... ገጽ ፩፻፬

## CONTENTS

Proclamation No. 18/1996
International Development Association Loan Agreement for partly financing the National Fertilizer Project Ratification Proclamation ............... Page 104

### አዋጅ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፹፰

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለብሔራዊ የማዳበሪያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር ፹፪ ሚሊዮን ፱፻ ሺህ (ሰማንያ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) ወይም ፩፻፳ ሚሊዮን (አንድ መቶ ሃያ ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፭ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመ በመሆኑ ፤

ይህንን የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያፀደቀው ስለሆነ፤

በህገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፲፪ መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለብሔራዊ የማዳበሪያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO.18/1996

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of eighty-two million nine hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 82,900,000) for partly financing the National Fertilizer Project, was signed in Washington D.C., on the 29th day of September, 1995;

WHEREAS, the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 13th day of February, 1996;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55/12 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for partly financing the National Fertilizer Project Ratification Proclamation No.18/1996."

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፳፱/፲፱፻፺፭ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመው ቁጥር ፪ሺህ ፯፻፵ ET የብድር ስምምነት ነው ።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘው ፹፪ ሚሊዮን ፱፻ሺህ ኤስ·ዲ·አር (ሰማንያ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No.2740 ET signed in Washington D.C., on the 29th day of September, 1995 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Internaional Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of eighty-two million nine hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 82,900,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 13th day of February, 1996.

Done at Addis Ababa, this 13th day of February, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE